የዓመቱ ጥያቄዎች

1. ትርጉም

ጥምቀት በጽርዕ ቋንቋ ኤጲፋኒ በግእዝ አስተርእዮ ነበእግርኛ መገለጥ ይባላል። ቃሉ በቀጥታ ሲተረጉም በውኃ ውስጥ ገብቶ መውጣት፣ መነከር፣ መዘፈቅ ፣መጥለቅ ማለት ነው። በምሥጢራዊ ትርጓሜ ግን ጥምቀት ከሰባቱ ምሥጢራት ቤተ ክርስቲያን /ጥምቀት፣ ሜሮን፣ ቁርባን፣ ንስሐ፣ ክህነት፣ ተክሊልና ቀንዲል/ አንዱና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኒቆዲሞስ በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ 3 ቁጥር 5 ላይ«...ሰው ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ ወደ እግዚአ ብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም» ብሎ እንደተናገረው ከውኃና ከመንፈስ ተወልዶን የሥላሴን ልጅነት የምናገኝበት፣ መንግሥተ ሰማያት የምንገባበት፣ ኃጢአታችን የሚደመሰስበትና ድኅነትን የምናገኝበት ወቢይ ምሥጢር ነው። ጥምቀት በምሥጢረ ሥላሴና በምሥጢረ ሥጋዌ አምኖ ለሚቀበለው ሰው ሁሉ ለኃጢአት መደምሰሻ ፣ከሥላሴ የጸጋ ልጅነትን ለመቀበልና የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ የተሰጠ ልዩ የሕይወት መንገድ ነው።

2. አመጣጥ

የምሥጢረ ጥምቀት መሥራቹ ራሱ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ነገር ግን ከጌታችን ጥምቀት በፊት አይሁድ ለመንጻትና ለኃጢአት ሥርየት /ይቅርታ/ የሚጠመቁት ጥምቀት ነበራቸው። ይኸውም እግዚአብሔር በሪድ ኤት በሚገለጥባቸው የተቀደሱ ዕለታትና ቦታዎች ሁሉ ሰውነትንና ልብስን ማጠብ ፣የእግዚአብሔር ቤት መገልገያ የሆኑ ዕቃዎችን ሁሉ ማጠብ ማንጻት ሥርዓትና ልምድ ነበር። የእግዚአብሔርም ፈቃድ ያለበት አሠራር ነበር። ወደ ቤተ እግዚአብሔርም ከመቅረባቸውና ለተቀደሰው አገል ግሎት ከመግባታቸው አስቀድመው እግሮቻቸውንና እጆቻቸውን የመታጠብ ግዴታም ነበራቸው። ሰውነታቸውን የመታጠብ ግዴ ታም ነበራቸው። ሰውነታቸውን ከአፍ አዊ /ከውጫዊ/ እድፍ በማጠብና ንጹሕ በማድረግ በባሕርዩ ንጹሐና ቅዱስ በሆነው አምላክ ፊት ሙሉ ሣዊ ሕይወትን ንጹሕ አድርጎ የመቅ ረብን ሥርዓትና ምሥጢር የሚያመ ለክት ልማድ ነበር።

«አሮንንና ልጆቹንም ወደ መገናኛ ቸው ድንኳን ታቀርባቸዋለህ፤ በውኃም ታጥባቸዋለህ፤ ሙሴም አሮ ንና ልጆቹን አቀረበ። በውኃም አጠ በቸው» /ዘጸ. 29÷4፣ ዘሌ.8÷6/። ዮሐንስ በዮርዳኖስ በኢየሩሳሌም ይሁዳ ለአውራ ጃዎች ከጌታ ቀደም ብሎ ተልኮ «መንግ ሥተ ሰማያት በልጅነት ልጅነት በእምነ ትና በጥምቀት ልትሰጥ ቀርባለችና ንስሐ ግቡ፣ ከኃጢአትና ከበደል ተመ ለሱ» እያለ ለኃጢአት ሥርየት ለንስሐ የጠምቅ ነበር። ብዙ ሰዎችም ኃጢ አታቸውን እየተናዘዙ ከሱ ይጠመቁ ነበር።

በብሉይ ኪዳን ዘመን በርከት ያሉ የጥምቀት ምሳሌዎችን እናገኛለን። ከእነዚህ ውስጥ የተመለከትን ለመመ ልከት፡-

1ኛ. አብርሃም ዮርዳኖስን ተሻ ግሮ ወደ መልከ ጼዴቅ መሄዱ የጥም ቀት ምሳሌ ነው። አብርሃም የምእመናን ፣መልከ ጼዴቅም የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌዎች ናቸው። ዘፍ.14÷17።

2ኛ. ኢዮብ በዮርዳኖስ ተጠምቆ ከደዌው ተፈውሷል። ይህም ምእመናን ተጠምቀው ከደዌ ሥጋ ከደዌ ነፍስ የመፈወሳቸው /ከመርገመ ሥጋ ከመር ገመ ነፍስ / የመዳናቸው ምሳሌ ነው።

3ኛ. ንዕማን ሶርያዊ ተጠምቆ ከለምጹ ድኗል። 2ኛ.ነገ.5÷14። ይኸ ኛውም ምእመናን ተጠምቀው ከመር ገመ ሥጋ ከመርገመ ነፍስ የመዳና ቸው ምሳሌ ነው።

4ኛ. የኖኅ መርከብ የጥምቀት ምሳሌ ነው። ዘፍ.6÷13። ይኸንንም ሐዋ ርያው ቅዱስ ጴጥሮስ «ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፍስ በውኃ የዳኑብት መርከብ ሲዘጋጅ የእግዚአብሔር ትዕግሥት በኖኅ ዘመን በቆየ ጊዜ ደግሞ አልታ ዘዙም። ይህም ውኃ ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድንናል። የሰውነትን እድፍ ማስወገድ አይደለም፣ ለእግዚአ ብሔር የበጎ ኅሊና ልመና ነው እንጂ» ሲል ተርጉሞታል። 1ኛጴጥ.3÷20።

5ኛ. እሥራኤል በደመና ተጋር ደው ቀይ ባሕርን መሻገራቸው የጥም ቀት ምሳሌ ነው። ዘፍ.14÷15። ይኸ ንንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «አባ ቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ። ሁሉም በባሕር መካከል ተሻገሩ። ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመ ናና በባሕር ተጠመቁ።» ሲል ተርጉሞ ታል። 1ኛ.ቆሮ.10÷2።

6ኛ. ለአብርሃም ሕግ ሆኖ የተ ሰጠው ግዝረት የጥምቀት ምሳሌ ነው። አብርሃም ካረጀ በኋላ ቢገረዝም ልጆ ቹ ግን በተወለዱ በስምንተኛው ቀን እንዲገረዙ እግዚአብሔር አዘዘ ነበር። ዘፍ.17÷9። ይኸንንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «በእጅ ባልተደረገ መገረዝ በእርሱ ሆናችሁ ደግሞ ተገረዛችሁ» ሲ ል ተርጉሞታል። ቆላ. 1÷11። እንግዲ ህ ግዝረት የጥምቀት ምሳሌ በመሆኑ በአራቱ ዘመን ቀን ተወስኖ ሕፃናቱ ይገረዙ እንጂ ነበር በአዲስ ኪዳንም ቀን ተወስኖ ሕፃናት ወንዶች በተወ ለዱ በአርባኛው ቀን ሴቶቹ ደግሞ በተወለዱ በሰማንያኛው ቀን ይጠመቃ ሉ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠ መቀው በ5531 ዓመተ ዓለም፣ በዘመነ ሉቃስ ግክሰኛ ጥር 11 ቀን ከሌሊቱ በ10ኛው ሰዓት ነበር። /ዮሐ.ነ፲ አንቃጽ 19 ድስቅ.29፣ ተረፈ ቄርሎስ በተጠ መቀም ጊዜ ዕድሜው 30 ዓመት ከ13 ቀን ነበር። ሉቃ.3÷23።

ለመሆኑ ጌታችን ለምን በ30 ዓመቱ ተጠመቀ?

በብሉይ ኪዳን ሥርዓትና ልማድ ካህናት ለቢተ እግዚአብሔር ተልዕኮና መንፈሳዊ አገልግሎት ከ30 ዓመት ዕድሜ በፊት እደባባይ አይወጡም ነበ ር። እድሜ አስፈላጊ እንኳ ቢሆን ከ20 እና 25 ዓመት አስቀድሞ ለአገልግሎ ት መሰየም ልማድ አልነበረም። የቤተ እግዚአብሔር አገልጋዮች በዕድሜና በዕውቀት የበሰሉ፣ በጠባይና በሥራ ልምድ የተፈተኑ ተልእኮአ ቸውን በብቃት ለመወጣት በተገልጋዩ ሕዝብ ዘንድ የተመሰከረላቸው መሆን ነበረባ ቸው ። ዘኁ. 4÷3፣ 1ኛ ዜና. መዋ. 23÷24፣ ዕዝ. 3÷8፣ 1ኛጢሞ. 3÷6-10።

ያንን ሥርዓት ለመፈጸም ጌታ ችን የተጠመቀውና ለትምህርተ ወን ጌል የተገለጠው በ30 ዓመቱ ነበር። ዮሐንስ መጥምቅም የጌታን መምጣት ለማወጅ በዮርዳኖስ ይሁዳ ምድረ በዳ ዎች ወጥቶ የታየው ከ30 ዓመት ዕድሜ ው በኋላ ነው።

ሌላው ወቢይ ምክንያት የሰው ሁሉ መጀመሪያ አዳም የ30 ዓመት ጎልማሳ ሆኖ ተፈጥሮ በ40ኛ ቀን ተሰ ጥቶት ያስወሰደውን ልጅነቱን /የባሕ ርይ አምላክነቱን / ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ለማስመስከር የአዳምን ልጆች የዕዳ ደብዳቤ ለመደምሰስና በስሕተት የጠፋውን የልጅነት ክብር ለመመለስ ነው። ጌታ ተጠምቆ ከውኃው ከወጣ በኋላ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ በማረፉ አብ በደ መና ይህ ልጄ ነው» ብሎ ሲመሰክ ርለት ምሥጢረ ሥላሴ እንድትና ሦስትነት በጉልህ ተረጋግጧል። ማቴ. 3÷16።

ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ ሲሆን በአ ገልጋዩ በቅዱስ ዮሐንስ እጅ ይጠመቅ ዘንድ በፍጹም ትኅትና ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ። ይህንንም ያደረገልን አብነት ሊሆነን ነው። ምክንያቱም

ጌታችን ቅዱስ ዮሐንስን «መጥተህ አጥምቀኝ» ብሎት ቢሆን ኖሮ ነገ ተነ ግ መዲያ ነገሥታቱና መኳንንቱ ካህና ቱን መጥታችሁ አጥምቁኝ» ቢሉ ነበ ር። ስለዚህ እንዲህ እንዳይሆን ነው ጌታችን «ጊታ» ሊሆን በባሪያዬ እጅ እንደተጠመቅህ እናንተም ወደ ቤተ ክርስቲያን ሂዳችሁ በካህናት እጅ ተጠ መቁ ሲል ነው። ቅዱስ ዮሐንስ ጌታችን በእርሱ እጅ ለመጠመቅ ወደ እርሱ በመጣ ጊዜ «እኔ ባሪያህ በአንተ በጌታዬ እጅ ልጠመቅ ያስፈልገኛል እንጂ አንተ በእኔ በባሪያህ እጅ ትጠ መቅ ዘንድ እንዴት ወደ እኔ ትመጣ ለህ ?» አለው። ጌታችንም መልሶ «አሁንስ ፍቀድልን፣ እንግዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና ትዝቢተ ነቢ ያትን እንዲህ ልንፈጽም ያስፈልጋል» አለው። በዚህን ጊዜ ቅዱስ ዮሐንስ ጌታችንን አጠመቀው። በዚህም «መጥ ምቀ መለኮት» ተብሎ የቅዱስ ዮሐንስ ገናንነቱ ይነገራል፣ ጌታችንም በባሪ ያው እጅ በመጠመቁ ፍጹም ትዅት ኖው ይነገርለታል።

ጌታችን በዮርዳኖስ የተጠመቀው ልጅነትን ያምታሰጥ ጥምቀትን ባርኮ ቀድሶ ሊሰጠን እንጂ ክብር እንዲሆነው አይደለም። ምክንያቱም እርሱ እክብር አይል ክቡር አለድቅ አይል ጻድቅ ነውና።

ቅዱስ ዮሐንስ ጌታችንን ምን አያለ እንደሚያጠምቀው አልገባውም ነበር። በዚህም ምክንያት ጌታችንን «ጌታ ሆይ ሌላውን በአንተ ስም በባሕርይ አባትህ በአብ ስም፣ በባሕርይ ሕይወትህ በመ ንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቃለሁ። አንተ ንስ የማጠምቀው በማን ስም ነውን ብሎ ጠየቀው ጌታችንም «ወልዱ ለቡሩ ክ ከሃቴ ብርሃን ተሠሃለነ እግዚአ፣ አንተ ካህኑ ለዓለም በክመ ሢመቱ ለመልክ ጼዴቅ፣ የቡሩክ አብ ልጅ ቡሩ ክ ወልድ ብርሃንን የምትገልጥ ይቅር በለን። እንደ መልክ ጼዴቅ ከህንት አን ተ ለዘለዓለም ክህን ነህ» እያልክ አጥ ምቀኝ ብሎታል።

ጌታችን በተጠመቀ ጊዜ ምሥጢረ ሥላሴ ተገልጧልና። መንፈስ ቅዱስ በተ ለየ አካሉ በርግብ አምሳል ወረደ፣ አብ ም በተለየ አካሉ በደመና ሆኖ በማዕከለ ድርዳኖስ የቆመውን ኢየሱስ ክርስቶስ ስን መለኮትን ከሥጋ ሳይለያይ አንድ አድ ርጎ «የምወደው ልጄ ይህ ነው እር ሱን ስሙት» አለ። ምክንያቱም በተለየ አካሉ ሰው ሆኖ በየርዳኖስ የቆመው ኢየሱስ ክርስቶስ በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆኖአልና። በዚህን ጊዜ ሰማያት ተከፍተዋል። ተገልጦ የማያ ውቅ ሰማያዊ ምሥጢር ተገልጧል። የመንግሥተ ሰማያት በር ይከፈትላ ችኋ ልንማለት ነው።

ለመሆኑ ጌታችንና መድኃኒ ታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀትን ለምን በየርዳኖስ አደረገው?

በኢየሩሳሌም አካባቢ ብዙ ወን ዞች፣ ኩሬዎችና ሐይቆች መኖራቸው የታወቀ ነው። ጌታ ጥምቀትን የርዳኖስ ያደረ ገው ስለዚህ አስቀድሞ የተነገረው ትንቢ ት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ነው።

በሕር አይታ ሸሸች፣ የሮጻኖስም ወደ ኋላ ተመለሰች፣ አንተስ የርዳኖስ ወደ ኋላህ የተመለስኸው ምን ሁነሃል? አቤቱ ውኆች ዐዩህ፣ ፀየቱም ፈሩህ /የልቶ ችም ተነዋወጡ ውኆችም ጮሁ» መዝ 113/114÷3-4፣ 76÷16።

«ከዚህም ጋር ከላይ ምንጩ አንድ የሆነው ዮርዳኖስ ዝት ብሉ በደሴት ተከፍሉ እንደገና ዝት ብሉ እንደሚ ገናኝ በግዘራትና በቀልፈት /በመገዝርና ባለመገ ዘር /ተለያይተው የነበሩ ሕዝብና አሕዛብ መላው የአዳም ልጆች በጌታ ጥምቀት አንድ መሆናቸውን የሚገልጽ ትርጉም አለው። አሥራኤል ዮርዳ ኖስን ተሻግረው ምድረ ርስት ገብተዋል። ያመኑ የተጠ መቁ ምእመናንም በጥምቀት ገነት መንግ ሥተ ሰማያትን ይወርሳሉ። ዮሐ. 21÷15።

ከላይ ከቀረቡት ታሪኮች ለመረዳት እንደምንችለው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀው በዮሐንስ እጅ ነው። ለምን?

ቅዱስ ዮሐንስ በኃጢአት የተጸደ ቀው ሁሉ ንስሐ ገብተው የተዘጋጀላ ቸውን መንግሥት ወራሾች ይሆኑ ዘንድ «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» እያለ ሲሰብክ ነበር። ይህ «መንግ ሥተ ሰማያት በልጅነት፣ ልጅነት ደግሞ በሃይማኖት ልትሰጥ ቀርባለችና ከኃጢአት ተለይታችሁ፣ ከበደል ርቃችሁ ቅረቡ» ማለት ነው። በነቢያት እንደ ተነገረውም «የእግዚአብሔርን መንገድ አዘጋጁ፣ ጥርጊ ያውንም አቅኑ» እያለ ድምጹን አብ ምቆ ሰብኳል። ምሥጢሩንም በመጣ ጊዜ ተራ ራውና ኮረብታው ተነዶ፣ ጎድጓዳው ተመ ልቶ፣ ሥሩ ተነቅሶ፣ ደንጊያው ተለቅሞ ለፈረስ ለሰረገላ እንዲመች ተደልድሎ እንደሚቆይ ሁሉ እናንተም የእግዚአብሔ ር ማደሪያ የሆነውን ሰውነታችሁን ከኃጢ አታችሁ ንጹሕ አድርጋችሁ ጠብቁ ማለት ነው።

ቅዱስ ዮሐንስ ከንስሐው ሰብኩት በተጨማሪም ዘመን የማይቆጠርለት ሲ ሆን ለጋን በመልበሱ ዘመን ተቆጥሮ ሮለት ከእርሱ በኋላ ስድስት መር ዘግይቶ ስለሚመጣው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነ ትም ሰብኳል፣

«እኔስ ለንስሐ በውኃ አጠም ቃችኋለሁ፣ ጫማውን እሸከም ዘንድ የ ማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል። እርሱ በመን ፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃች ኋል» መን ሹም በእጁ ነው፣ አውድማውንም ሰንዴ ውንም በጎተራው ይከታል፣ ፈጽሞ ያጠ ራል፣ ስንዴውንም በጎተራው ይከታል፣ ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥ ለዋል» ማቴ. 3÷11፣ ዮሐ.1÷26።

እኔ ክርስቶስ አይደለሁም፣ ነገር ግን ከእርሱ በፊት ተልኬአለሁ እንዳ ልሁ ራ ሳችሁ ትመሰክሩልኛላችሁ። ሙሽራይቱ ያለችው እርሱ ሙሽራ ነው፣ ቆሞ የሚሰ ማው ሚዜው ግን በሙሽራው ድም ጽ እጅግ ደስ ይለዋል። እንግዲህ ይህ ደስታዬ ተፈጸመ። እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል። ከላይ የሚ መጣው ከሁሉ በላይ ነው፣ ከምድር የሚሆነው የም ድር ነው፣ የምድርንም ይናገራል። ከሰ ማይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው። አባት /አብ ልጁን /ወልድን ይወዳል። ሁሉንም በእጁ ሰጥቶታል። በልጁ የሚ ያምን ግን ያለማዘለአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አይ ደለም» ዮሐ.3÷28።

በዚህ ስብሰባችን ምስክርነቱ የተገ ለጸ በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ። ከዚህም ጋር ጌታ ዮሐንስ መጻሰበት ቺጾ ተጠ መቀ እንጂ ዮሐንስ ወደሱ እንዲመጣ አላደረገም። ይህም በዚህ ዓለም ህብ ትና ሥልጣን ያላቸው ሰዎች ሁሉ ክህና ትን በየቢታችን እያመጣችሁ አጥምቁን የማለት ልምድ እንዳይኖር ሥርዓት መመስረትና ጌታ መምህሪ ትሕትና መሆኑን የሚያመለክት ነው።

3. የበዓሉ አከባበር

ይህ የዓለም መድኃኒት የጌታ ችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት መታሰቢያ በዓል በመላው ዓ ለም በክርስቲያኖች ይከበራል። በሳሉ የሚከበርበት መሠረታዊ ሥልአከት ተመሳሳይ ቢሆንም የአከባበሩ ይዘት፣ ሥርዓትና ትውፊት እንደ የሀገሩ ባሕ ልና እንደየ አብያተ ክርስቲያናቱ እምን ትና ሥርዓት የተለያየ መልክ አለው።

የጥምቀት በዓል በኢትዮጵያ እርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዓ መታት ቡዳት ከሚከበሩባት ወበይት በዓ ላት አንዱ ነው። በአጻምና ሐዋን ሰብ አዊ ተፈጥሮ አንድ ለሆነው ሰው ሁሉ ደኅንነት የሰጠን ሥጋ ተዋሕዶ በተገ ለጠው በኢያሱስ ክርስቶስ ደም የታን ጸችው አሐቲ ቤተ ክርስቲያን በሰዎች የተለያየ አመለካከትና የእምነት ትርጉም ዛሬ በየአህጉሩና በየጎጡ ተከፋፍ በተከፋ ሰሞች ብትጠራም የቅዱስ ክርስ ቅናውን መሠረት ሳትለቅ፣ ከሐዲምት አበው በተላለፈው እምነትና ሥርዓት ጸንታ የምትጓዘው የኢትዮጵያ እርቶዶ ክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተምቀ ችን በዓል የምታከብረውና የም ታከብ ረው በሌሎች ዘንድ በማንኛውም ቤተ ክርስቲያን በማይታይ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትውፊትና ሥርዓት ነው። በተለይ ጌታችን በፈለገ ዮርዳኖስ በእጹ ዮሐንስ የተጠመቀበትን ዕለት ከሃይማኖታዊ ታሪኩና መገ ፈሳዊ ምሥጢሩ አንጻር በ ማመልከት ጌታችን በዮሐንስ እጅ ሊጠ መቅ የዮሐንስ ጌታን ሊያጠምቅ ወደ ዮርዳኖስ እንደወረዱ ቤተ ክርስቲያን ታቦቷን ከመንበሯ አውጥታ ወደ ውኃ ምንጮች /መንዘሮች/ በመሄድ በልዩ መንፈሳዊ ሥርዓት ታከብራለች። ተከታ ዮም ምእመናን /ሕዝበ ክርስቲያኑም/ ከታቦታቱ ጋር በየአካባቢያቸው አብረው በመውጣት ለዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ያላቸውን እምነት፣ ፍቅርና አክብሮት ቢጋለ መንፈስ እየገለጡ በዓ ሉን በደማቅ ሥነ ሥርዓት የከብራሉ። ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ልዩ የሆነውን ይህን ሥነ በዓል ለመመ ልከት ከዓለም ዙሪያ የሚሰበሰቡ ሀገር ጎብኚዎች ብዙ ናቸው።

መልካም የጥምቀት በዓል።